የ10ኛ ክፍል

(ሁለተኛ ሳምንት)

የአማርኛ ቋንቋ ድምፆች በስርዓት ተዋቅረው ቃል ይመሰርታሉ፡፡ በዘመናዊ ሰዋሰው የቃል ክፍሎች በአምስት ይመደባሉ፡፡
እነሱም፡- ስም፣ ግስ ፣ ቅፅል ፣ ተውሳከ ግስ ና መስተዋደድ ናቸው፡፡

1. ስም ፡- የሰዎች ፣ የእንሰሳ ፣ የግዑዝና ረቂቅ ነገሮች መጠሪያ ሲሆን ፣ የሚከተሉትን የቅርፅ ና የአናባቢ ባህርይ ያሉት የቃል ክፍል ነው፡፡

~ / -ኦች/ የሚለውን አብዝ ምዕላድ ይወስዳል፡፡

. ሴት-ኦች

~ በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ባለቤት በመሆን ያገለግላል፡፡.አልጋው ተሰበረ፡፡

~ በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ ተሳቢ በመሆን ያገለግላል፡፡

ምሳሌ.መምህሩ ተማሪውን መከረ።

~ ጠቃሚ ወይም መጣኝ መስተፃምር ቀድሞ ሊገባ ይችላል። ምሳሌ ያ በሬ አርጅቷል፡፡

~ አይነትን የሚገልፅ አንላማሽ ይወስዳል፡፡ ምሳሌ-ጥቁር ቀሚስ እወዳለሁ፡፡

ከላይ ከቀረቡት የተሰመረባቸው ቃላት በሙሉ የቃል ክፍላቸው ስም ነው።

2. ግስ ፡- ድርጊትን አመልካች የሆነ ቃል ክፍል ነው ። በአገባቡም በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ ይገኛል።

ግስ በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ ከመጣ ማሰሪያ አንቀፅ ይባላል።

-ግስ በሌሎች የቃል ክፍሎች የምንለይበት ሁለት ዋና መስፈሪያዎች አሉት።

-አንደኛው በአገባቡ በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ መገኘቱ ሲሆን፣

- ሁለተኛው ቅርፁ ነው።

ለምሳሌ ፦ ሰላም ደብተር ገዛች ።

ገዛ-ኣች

ኣች - ባለቤት አመልካች ቅጥያ ነው።

3. ቅፅል (ስም ገላጭ) ፦ ስምን ቀድሞ በመግባት የስም ባህርይ ፣ መልክ ፣ መጠን ፣ አይነት ወዘተ የሚገልፅ የቃል ክፍል ነው።

ክፍሎቹ ነባርና ውልድ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ።

ነባር ቅፅል ፦ ከሌላ ቃል ያልተመሰረተ ከመጀመሪያ ጀምሮ በቋንቋው ያለ ቃል ነው። ለምሳሌ ፦ ደግ ፣ክፉ
ውልድ ቅፅል ፦ ከሌላ ቃል የተወሰደ ቅፅል ሲሆኑ ፣ ለምሳሌ ፦ አይናማ ፣ተራራማ

4.ተውሳከ ግስ ፦ ግስን ለመግለፅ የሚገባ ቃል ወይም ሀረግ፣ ተውሳከ ግስ ወይም የግስ ገ ላጭ ይባላል ።ግስን ከጊዜ፣ከቦታ ፣ከሁኔታ ወዘተ. አንፃር የሚያነላ ነው።

ነባር ተ/ግስ ፦ ዛሬ ፣ አሁን ፣ አምና ፣በፍጥነት ወዘተ.

ውልድ ተ/ግስ ፦ ክፉኛ፣ ጅልኛ፣ዋነኛ ወዘተ.

5. መስ ተዋደድ ፦ተናጠላዊ ትርጉም የሌላቸው ሲሆኑ ፣ ትርጉም የሚሰጡት ከሌላ ቃል ጋር ተቀናጅተው ነው።

መስተዋድዶች ከስምና ከግስ ጋር ሲቀናጁ የተለያዩ ሰዋስዋዊ ተግባራት ይኖራቸዋል።

ለምሳሌ ፦ 1. ስለ ተማሪ
ከ ቤት } ከስም ጋር ሲቀናጅ

2 ስለ ደከመ
እንደ ደረሰ } ከግስ ጋር የተቀናጀ

-መስተዋደዶች ስለተለያዩ ሰዋስዋዊ ተግባር ኣይለውጡም።

- መስተዋደዶች ሌላ ቃል ኣይመሰርቱም ፤ ከሌ ላ ቃል ም ኣይመሰረቱም።

የመልመጃ ጥያቄዎች

በሳጥኑ ውስጥ ተዘበራርቀው የተቀመ ጡትን ቃላት በየቃል ክፍሎቻቸው መድቧቸው::

ሁል ጊዜ በ አመነች የተንሻፈፈ ትግል ቀለበ ስለ	ዘመናዊ ድንገት መለሱልን ምግብ ነገረኛ ትምህርት ሓይለኛ	ጌጦች አጭር ዘወትር ከ ወደ መብራት ቆሎ ወገቧ	እንደ ቆረጠ እንደገና አዲስ እስከ ለገሰ

ምሳሌ፡-

ስም	ቅፅል	ግስ	ተውሳከ ግስ	መስተዋደድ
ምግብ	ዘመናዊ	ቀረበ	ድንገት	ከ